# በኦቶማቲክ መንገድ የሚደረግ የከተማ የኤሌክትሪክ ፕሮግራም ምዝገባ ማስታወቅያ

ሰኔ (June) 23 ቀን 2026

**<u>በ Cambridge Community Electricity፤</u>** የከተማችን በቡድን ኤሌክትሪክ የመግዛት ፕሮግራም፤ የኤሌክትሪክ ሂሳብዎ በኦቶማቲክ መንገድ እንዲመዘገብ ብቁ ያደርጋል። የኤሌክትሪክ ሂሳብዎ ቁጥር ከዚህ ጋር ተያይዞ በሚገኘው የመልስ ካርድ ውስጥ ይገኛል።

በ Cambridge Community Electricity መሳተፍ ማለት፤

- በ Eversource የኤሌክትሪክ አቅርቦት ሂሳቦ ላይ ያለው የኤሌክትሪክ ዋጋ ለአንድ ኪሎዋት ወደ **14.48 ¢/kWh** (ሳ/ኪሎዋት) ይቀየራል። ይህም Eversource ለመኖርያ ቤቶችና ለትናንሽ ንግድ ቤቶች በነሓሴ (August) 1 ቀን ከሚያስከፍለው የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋ **ዝቅ** ያለ ነው።

  የ Eversource ዋጋዎች በየግዜው ስለሚቀያየሩና በመጪው ግዜያት ዋጋዎቹ ምን ያህል እንደሚሆኑ በትክክል ስለማይታወቅ፤ ከ Eversource ጋር ወደፊት የገንዘብ ቁጠባ (savings) ለማድረግ ዋስትና የለም።
- አዲሱ ዋጋ እስከ **ጥር (January) 2029** ድረስ ቋሚና የተረጋጋ ሆኖ ይቆያል።
- እርሶም የ Eversource ደንበኛ መሆንዎን ይቀጥላሉ፤ Eversource ም የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ መሆኑን ይቀጥላል፤ የኤሌክትሪክ ሂሳቦንም ይልክሎታል።
- ለአዲሶች የሚታደሱ የሃይል ፕሮጄክቶች በቀጥታ ድጋፎን ይሰጣሉ። ዝርዝሩ በስተጀርባ በኩል ይገኛል።

አዲሱ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋዎ፤
**14.48 ¢/kWh**

ከፕሮግራሙ ለመውጣት የመጨረሻው ቀን፤
**ሐምሌ (July) 27 ቀን 2026**

የደንበኞች እገዛ:
**844-379-9934**

ተጨማሪ መረጃና የራስ አገልግሎት (self service):
**CambridgeMA.gov/enrollCCE**

## ውሳኔው የእርሶ ነው። ለእርሶ ትክክል ነው የሚሉትን ይምረጡ።

▶ **<u>መሳተፍ ከፈለጉ፤ ምንም እርምጃ አይውሰዱ።</u>** በ14.48 ¢/kWh ዋጋ በኦቶማቲክ መንገድ በ Standard Green ይመዘገባሉ፤ የኤሊክትሪኮን 75% ውንም ከሚታደሱ አዲስ ምንጮች ያገኛሉ።

▶ **<u>የፕሮግራሞን አማራጭ ለመቀየር ከፈለጉ፤</u>** 100% ውን ኤሊክትሪኮን ከሚታደሱ አዲስ ምንጮች ለማግኘት ከፈለጉ በ 100% Green ይመዝገቡ። የፕሮግራሙን ዝቅተኛውን ዋጋ ለማግኘት ከፈለጉ ደግሞ Economy ን ይምረጡ።

| 14.90 ¢/kWh | 14.48 ¢/kWh | 13.77 ¢/kWh |
|---|---|---|
| 100% GREEN | STANDARD GREEN | ECONOMY |
| 100% ከአዲሶቹ የሚታደሱ ምንጮች | 75% ከአዲሶቹ የሚታደሱ ምንጮች | ዝቅተኛው የፕሮግራሙ ዋጋ |
| **አማራጭ** | **ኦቶማቲክ ምዝገባ** | **አማራጭ** |

የCambridge Community Electricity ዋጋዎች እስከ **ጥር (January) 2029** ድረስ ቋሚ ሆነው ይቆያሉ። የ Eversourceን ዋጋዎች ለማወቅ በስተጀርባ ይመልከቱ።

▶ **<u>ለመሳተፍ የማይፈልጉ ከሆነ፤</u>** በፕሮግራሙ መሳተፍ ግዴታ አይደለም። ከCambridge Community Electricity ለመውጣት ከፈለጉ የሚከፍሉት ገንዘብ ወይም መቀጮ የለም። ባፈለጉት ግዜም መውጣት ይችላሉ። በኦቶማቲክ መንገድ መመዝገብን ለማስወገድ፤ መውጣት እፈልግለሁ የሚል ጥያቄዎን ከ **ሐምሌ (July) 27 ቀን 2026** በፊት ያስገቡ። ፕሮግራሙን ለመሞከር ከፈለጉ ደግሞ ከሞክሩት በኋላ በማንኛውም ግዜ መውጣት ይችላሉ።

**የተለየ የፕሮግራም አማራጭ ለመምረጥ ወይም ከፕሮግራሙ ለመውጣት CambridgeMA.gov/enrollCCE ን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 844-379-9934 ወደ ደንበኞች እገዛ ክፍል ደውለው ከከተማይቱ የፕሮግራም አማካሪዎች ጋር ይገናኙ።**

## የCambridge Community Electricity ዋጋዎችን ከ Eversource የኤሌክትሪክ አቅርቦት ዋጋዎች ጋር አወዳድሩ፤

| | | በኦቶማቲክ መንገድ የሚደረግ ምዝገባ ▼ | | ከፕሮግራሙ ከወጡ ▼ |
|---|---|---|---|---|
| **የ Cambridge Community Electricity ዋጋዎች** | 100% GREEN | STANDARD GREEN | ECONOMY | EVERSOURCE BASIC SERVICE |
| **ዋጋ** | **14.90 ¢/kWh** | **14.48 ¢/kWh** | **13.77 ¢/kWh** | **17.323 ¢/kWh** – መኖርያ ቤቶች<br>**16.761 ¢/kWh** – አነስተኛ ንግድ ቤቶች<br>**12.031 ¢/kWh** – መካከለኛና ትላልቅ ንግድ ቤቶች |
| **የዋጋዎች ግዜ** | ምዝገባ – ጥር (January) 2029 | ምዝገባ – ጥር (January) 2029 | ምዝገባ – ጥር (January) 2029 | ከነሐሴ (Aug.)1 ቀን 2026 እስከ ጥር (Jan.) 31 ቀን 2027 - መኖርያ ቤቶችና ትናንሽ ንግድ ቤቶች፡ ከነሐሴ (Aug.)1 ቀን እስከ ጥቅምት (Oct. ) 31 ቀን 2026 - መካከለኛና ትላልቅ ንግድ ቤቶች |
| **ከአዲስ የሚታደሱ ምንጮች የሚገኝ ኤሌክትሪክ (ከጠቅላላው %)*** | | | | |
| በ Cambridge ** የተጨመረ | 70% | 45% | – | – |
| በክፍለሃገሩ ሕግ የሚጠየቅ (የኤም-ኤ (MA) Class I RECs) | 30% | 30% | 30% | 30% |
| **ከሚታደሱ አዲስ ምንጮች** | **100%** | **75%** | **30%** | **30%** |

* በሰንጠረዡ ከሚታየው የሚታደስ ኤነርጂ መግዛት በተጨማሪ፤ የፕሮግራሙ የኤሌክትሪክ አቅራቢ የሚታደስ ኤነርጂ የምስክር ወረቀት (አር-ኢ-ሲ-REC) ከሌሎች ንጹህ/ የተጣራ ወይም የሚታደስ ምንጮች እንዲገዛ የክፍለሃገሩ ህግ ይጠይቃል። የሚገዛው ኤነርጂ የተሳታፊውን 39% ውን የኤሌክትሪክ ፍጆታ መሸፈን አለበት።

** እነኚህ በ አር-ኢ-ሲ (REC) የሚታወቁ የምስክር ወረቀቶች፤ በፕሮግራሙ በሚደገፉና ከኑ ኢንግላንድ ( New England ) ውጪ ከሆኑ ሁለት የሚታደሱ የኤነርጂ ፕሮጀክቶች መገዛት አለባቸው።

## ተጨማሪ መረጃ፤

- **የኤሌክትሪክ አቅራቢዎ Direct Energy Services, LLC ("Direct Energy") ይሆናል።** በክፍያ ወረቀትዎ/ሂሳብዎ ላይ የሚያዩት ስም "Cambridge Comm Elec Direct Energy ነው። ግን ዋነኛው የኤሌክትሪክ ዝምድናዎ ወይም ግንኙነትዎ ከ Eversource ጋር መሆኑን ይቀጥላል። የኤሌክትሪክ መቋረጥ ሲያጋጥም ወደ እነሱጋ መደወሎን ይቀጥላሉ። Eversource የኤሌክትሪክ ሂሳቦን ለእርሶ መላኩን ይቀጥላል። እንደ አንድ የኤሌክትሪክ ፕሮግራሙ ተሳታፊ መጠን፤ የሚደርሶት የኤሌክትሪክ ሂሳብ ይህ ብቻ ነው።
- **የፕሮግራሙ ተሳታፊዎች በሙሉ አዲስ የሚታደሱ የኤነርጂ ፕሮጄክቶችን በቀጥታ የሚደግፉ ናቸው።** በ Cambridge በGraham and Parks Elementary School የተደረገውን ከጸሃይ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ግኝት እድገትን ደግፈዋል። በተጨማሪም፤ በ Standard Green እና በ 100% Green ውስጥ ለሚገኙት ደንበኞች/ተሳታፊዎች፤ ከተማው ከ Illinois ከጸሃይ የሚገኝ ኤነርጂ እና ከ North Dakota በንፋስ የሚሰሩ ፕሮጄክቶንች ለመግዛት ቁርጠኛነቱን አሳይቷል። ይህ ቁርጠኛነቱም እነኚህ ፕሮጄክቶች እንዲገነቡ ገፋፍቷል። እነኚህ ፕሮጄክቶች በኤሌክትሪክ መረቦች ላይ የተቋቋሙ ስለሆኑ፤ የኤሌክትሪክ ሃይል ለመፍጠር በኑ ኢንግላንድ (New England) ከሚገኙ ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች የበለጠ የካርበን ልቀት ያደርጋሉ፤ እነኚህ ንጹህ ፕሮጄክቶች ግን በነው ኢንግላንድ (New England) እንደሚደረግ ከፍተኛ የካርበን ልቀት እንዲወገድ ያደርጋሉ።
- **ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ለሚደረግ ቅናሽ ወይም የነዳጅ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ከሆኑ፤** እነኚህ ጠቀሜታዎች በ Cambridge Community Electricity ይቀጥላሉ።
- **በንብረትዎ ላይ ከጸሃይ የሚገኝ ኤነርጂ ለማመንጨት የሚችሉ መሳርያዎች ወይም ፓናሎች ካሎት ወይም በማህበረሰቡ የጸሃይ ኤነርጂ ፕሮግራም የሚሳተፉ ከሆነ፤** የጸሃይ ኤነርጂ ብድሮችንና/ወይም የጸሃይ ኤነርጂ ለማግኘት የሚደረጉ የማበረታቻ ክፍያዎች ማግኘትዎን ይቀጥላሉ። በ Cambridge Community Electricity በመሳተፎ ምክንያት የእነዚህ አሰላል (calculate) አይቀየርም።
- **ይህ ማስታወሻ ከደረሶትና ከሌላ የኤሌክትሪክ አቀባይ ጋር ውል ከተፈራረሙ፤** ውሎን የፈረሙት ይህ የመልእክት ዝርዝር (mailing list) ከመላኩ በፊት ሊሆን ይችላል። ከመረጡት የኤሌክትሪክ አቀባይ የሚያገኙት ኤሌክትሪክ እንዲቀጥልና ከአቀባዩ ጋር ያደረጉት የኤሌክትሪክ ውል ከግዜው በፊት በማቋረጥዎ፤ ሊደርስቦት ከሚችል የመቀጮ ክፍያ እንዲድኑ፤ ከ Cambridge Community Electricity መውጣት አለቦት።
- **ከግብር መክፈል ነጻ የሆነ ሂስብ ካሎት፤** ከግብር መክፈል ነጻ መሆንዎን የሚያመለክቱ ሰነዶችዎን ሁሉ ለ Direct Energy በመላክ፤ ከግብር መክፈል ነጻ እንዲሆኑ የሚጠይቅ ጥያቄዎን የማቅረብ ሃላፊነት የእርሶ ነውበበለጠ ለማወቅ CambridgeMA.gov/enrollCCE ይጎብኙ።
- **ይህ የኦቶማቲክ ምዝገባ ሞዴል ከክፍለሃገሩ ህግ ጋር የሚሄድ ነው፤** ከ200 የሚበልጡ በ Massachusetts ውስጥ የሚገኙ ከተሞች ተመሳሳይ ፕሮግራሞች አሏቸው። ሁሉም በአንድ ዓይነት መንገድ ይሰራሉ። ይሁንና እርሶ የግዴታ መሳተፍ የለቦትም። ምንም ገንዘብ ወይም መቀጮ ሳይከፍሉ በማንኛውም ግዜ ከፕሮግራሙ መውጣት ይችላሉ።

# የመውጫ መልስ የመስጠት ካርድ

## በ Cambridge Community Electricity ለመሳተፍ የማይፈልጉ ከሆነ፣ ከወደታች ይፈርሙ።

X ______________________________

**ፊርማ:** **ቀን:**

## ከፕሮግራሙ የመውጣት መመርያዎች

ምንም ዓይነት እርምጃ ካልወሰዱ፣ በኦቶማቲክ መንገድ በ Cambridge Community Electricity ውስጥ ይመዘገባሉ።

በፕሮግራሙ መሳተፍ ካልፈለጉ፣ ከፕሮግራሙ መውጣት አለቦት።

በፖስታ ለመውጣት ከፈለጉ፣
1. ይህንን ካርድ ይፈርሙ፣ ቀኑንም ይጻፉበት።
2. አብሮ በተላከሎት ፖስታ ውስጥ ካርዱን ያሽጉና ፖስታ ቤት ያስገቡ።

ይህ ካርድ፣ ስሙ በካርዱ ላይ በተጻፈው የመዝገብ ቤት ሹም (Customer of Record) መፈረም አለበት። በተጨማሪ ከፕሮግራሙ ለመውጣት ከፈለጉ ኦንላይን ወደ **CambridgeMA.gov/enrollCCE** በመግባት ወይም በስልክ ቁጥር **844-379-9934** በመደወል መውጣት ይችላሉ።

በፕሮግራሙ ውስጥ በኦቶማቲክ መንገድ ከመመዝገብዎ በፊት፣ መውጣት እፈልጋለሁ የሚለው ጥያቄዎና ይህንን የያዘው ፖስታ ወደ ፖስታ ቤት የገባው ከ **ሐምሌ (July) 27 ቀን 2026** በፊት መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ያዘለ መሆን አለበት። በፕሮግራሙ ለመሳተፍ ከመረጡ፣ የሆነ ገንዘብ ወይም መቀጮ ሳይከፍሉ ወደፊት በማንኛውም ግዜ መውጣት ይችላሉ።